# የእወደድ ባይ ፖለቲከኛነት /populist politics/

አለምነህ ለንደን

አራተኛው ዙር አገራዊና ክልላዊ ምርጫ መቃረብ ተከትሎ በምርጫው ለመወዳደር የሚፈልጉ ፓርቲዎች እጩዎቻቸውን በመመልመልና በማስመዝገብ፣ ከሌላው ጠርቲ ይለየናል በሕዝብ ዘንድም ተቀባይነት አግኝቶ ያስመርጠናል ያሉትን የፖለቲካ ፕሮግራም እና የምርጫ ማንፌስቶ በማዘጋጀትና በምርጫ ቅስቀሳው በመሳተፍ እንቅስቃሴ ተጠምደው ይታያል፡፡ ይህ ዓይነቱ እንቅስቀሴ ይበል የሚያሰኝና ሊበረታታ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ሕዝቡ ለምርጫ የሚቀርቡ ፓርቲዎች ፕሮግራምና ዓላማ ተረድቶ ቢመረጡና የመንግስትን ስልጣን ቢይዙ ምን ሊሰሩለት እንደሚችሉ ተገንዝቦ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ውሳኔ መስጠት ያስችለዋልና ነው፡፡ በሌላ በኩል ስንመለከት ደግሞ በእንዲህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ ነው ዴሞክራሲ ሊዳብርና ሥር ሊሰድ የሚችለው፡፡

በዚህ አጭር ፅሑፍ ለማውሳት የምፈልገው በቅርቡ የስምንት ጠርቲዎች ስብስብ የሆነው መድረክ በአዲስ አበባ ከተማ በ2002 ምርጫ ጠርቲውን ወክለው የሚወዳደሩ እጩ አባሎችን በማሰባሰብ በ2002 የመድረኩ አቋሞችን በተመለከተ ገለፃ በሰጠበት ወቅት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ እና አቶ ስዬ አብርሃ በሰጧቸው ማብራሪያዎች ዙሪያ ትንሽ ለማለት ፈልጌ ነው፡፡ የመድረክ እና የአንድነት ለፍትህና ዴሞክራሲ ፓርቲ ከፍተኛ አመራሮች የሆኑት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ እና አቶ ስዬ አብርሃ ወደ አነሷቸው ማብራሪያዎች አስተያየት ለመስጠት ከመሄዱ በፊት ግን ስለ ለውጥ መርህ በመጠኑ መግለጽ እፈልጋለሁ፡፡

ዓለማችን በማያቋርጥ የለውጥ እንቅስቃሴ ላይ መሆኗ የማይታበል ሃቅ ነው፡፡ እንዲያውም የማይለውጥ ጉዳይ ቢኖር ራሱ ለውጥ ብቻ ነው በማለት ብዙ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም ነው ታዲያ የአካባቢ ለውጥ/ የሙቀት መጨመር፣ የግግር በረዶ መቅለጥ፣ የበረሃማነት መስፋፋት/ የኤኮኖሚ ለውጥ፣ የቴክኖሎጂ ለውጥ/አሁን ባለንበት ዘመን ዓለማችን እጅግ እየተቀራረበች የመጣችው በኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ እና በትራንስፖርት ቴክኖሎጂ ፈጣን ለውጦች ሳቢያ ነው/ እና የፖለቲካ ለውጦች በዋናነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

የፖለቲካ ለውጥን ብናነሳ ምናልባት ከዛሬ 40 እና 50 ዓመት በፊት በዓለማችን ትልቅ ተቀባይነት አግኝቶ የነበረው የፖለቲካ አስተሳሰብ የኮሚዩኒስት ርዕዮተ ዓለም ነበር፡፡ ይህም የእዝ ኢኮኖሚ መርህን የሚሰብክ፣ የአንድ ጠርቲ አስተሳሰብን ብቻ የሚቀበል፣ የኮሚኒስት ጠርቲው ከሚያራምደው ሃሳብና ፖሊሲ ውጭ የሚመጣ አመለካከት በአጠቃላይ እንደጠላት የሚታይበት በመሆኑም ፀረ-አብዮትና ፀረ-ልማት እየተባለ የሚፈረጅበት እና ከዚያም አልፎ የአስተሳሰቡ አራማጅ የሆኑት የሚታሰሩበትና የሚገደሉበት ሁኔታ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከዛሬ ሃያ ዓመት ወዲህ በተለይ ከበርሊን ግምብ መፍረስ እና ከሶቪየት ሕብረት መፈራረስ ጋር ተያይዞ በዓለም ደረጃ ከፍተኛ የፖለቲካ ለውጥ ታይቷል፡፡ በመሆኑም የእዝ ኢኮኖሚ ሥርዓት በነፃ የገበያ ኤኮኖሚ ሥርዓት በብዙ አገሮች ተተክቷል፣ ከአንድ አምባገነናዊ ፈላጭ ቆራጭ የኮሙዩኒስት ፓርቲ በመላቀቅ የመድብለ ጠርቲ ሥርዓት በብዙ የዓለማችን አገሮች እውን ሆኗል፡፡ እናም በአጠቃላይ በፖለቲካ መስክ እጅግ ፈጣን ለውጦች ታይተዋል፡፡ በዓለምም ሆነ በአገር ደረጃ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን በሚገባ እየተከታተሉ ለዚህ በሚመጥንና በሚስማማ አኳኋን ለውጦችን ማድረግ ተገቢና አስፈላጊ መሆኑ እዚህ ላይ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ እንዲያውም እነዚህን ለውጦች ችላ ብሎ ከለውጦች ጋር አብሮ አለመጓዝ ነው አላዊነት፣ ደንታቢስነት ወይም ደግሞ ግትርነት ሊያሰኝ የሚችለው፡፡ እናም የፖለቲካ ጠርቲዎች የፖለቲካ ፕሮግራሞቻቸው ከወቅቱ የኤኮኖሚ፣ የሶሻል፣ የፖለቲካ፣ የቴክኖሎጂና የአካባቢ ለውጦች ጋር የሚስማማ መሆን አለመሆኑን በማየት ለዚህ የሚመጥንና ከዚህ ጋር አብሮ መጓዝ የሚችል የፖለቲካ ፕሮግራም ፖሊሲና ስትራቴጂ ይነድፋሉ፡፡ ይህን ካላደረጉ ግን ከወቅቱ ጋር አብረው መራመድ አልቻሉም ብቻ ሳይሆን በድን ሕይወት የሌላቸው ሆነዋል ማለት ነው፡፡

ከላይ ባጭሩ ስለ ለውጥ ፅንሰ ሃሳብና ምንነት ካነሳሁ ይህን ፅሑፍ ለመፃፍ ወደ አነሳሳኝ ርዕሰ ጉዳይ ልመለስ፡፡ ከላይ በጠቀስኩት የስብሰባ መድረክ የተከበሩ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ከኢ.ህ.አ.ዴግ አባልነታቸው እንዲለቁ ያስገደዳቸው ምክንያት ምን እንደነበር ማብራሪያ እንዲሰጡ ተጠይቀው የሰጡት ምላሽ በእጅጉ የሚያስገርም ነው፡፡ የተከበሩ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ምክንያታቸውን ሲያስረዱ ከኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ለመልቀቅ የወሰኑት ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ በተሃድሶ ፕሮግራሙ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ስርዓት ወይም ደግሞ በአቶ መለስ አገላለጽ «ነጭ ካፒታሊዝም» አካሂዳለሁ በማለቱና ይህ ደግሞ ለእርሳቸው ክህደት መስሎ ስለታያቸው

ከእንደዚህ ያለ «ውሽታም» ድርጅት ጋር መስራት ሞራላቸው የማይፈቅድላቸው መሆኑን ገልፀዋል። እዚህ ላይ ነው እንግዲህ ከለውጥ መርህ እና ከለውጥ ፅንሰ ሃሳብ ጋር የሚፃረር ምላሽ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የሰጡት ሁሉም ነገር በለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ ካለ ፖለቲካም በየጊዜው ይለወጣል ማለት ነው። ስለሆነም አንድ የፖለቲካ ጠርቲ ወይም ስብሰብ በአንድ ወቅት ይከተለው የነበረው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የሶሻል ወ.ዘ.ተ. አስተሳሰብ በዓለም እና በአገር ደረጃ በእነዚህ ከላይ በተጠቀሱት ጉዳዮች ዙሪያ ለውጥ ሲመጣ የግድ ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄድና የሚጣጣም ፕሮግራም መቀየስና መተግበር አስፈላጊ ነው። የተከበሩ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የታሪክ ትምህርታቸውን ለመከታተል ወደ ጀርመን ባመሩበት በ1960ዎቹ አጋማሽ ላይ በአገራችንም ሆነ በአፍሪካና በእስያ አገሮች በሰፊው ይቀናቀን በአንዳንዶቹም አገሮች ደግሞ ይተባበር የነበረው የግራ አስተሳሰብ ወይም የኮሚኒስት ርዕዮተ ዓለም ነበር። ከ18 ወይም 20 ዓመት በኋላ ግን የኮሙኒስት ርዮተ ዓለም ተንኮታኩቶ በምትኩ የነፃ ገበያ ኤኮኖሚ ሥርዓትና የመድብለ ጠርቲ ዴሞክራሲ እየጠናከረ የመጣበት ሁኔታ ነው የተፈጠረው። ስለሆነም ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ወይም አባል ድርጅቶች የትጥቅ ትግል እንቅስቃሴያቸውን ሲጀምሩ እና ትግሉን ሲመሩ ዋነኛው የፕሮግራማቸው መነሻ የኮሚኒስት ርዮተ የነበረ መሆኑ የማይካድ ጉዳይ ነው። ነገር ግን ዓለም እየተለወጠ ባለበት ሁኔታ በዚያው ልክም አገራችንም እየተለወጠች ባለችበት ሁኔታ ያንኑ የኮሙኒስት ርዮተ ዓለም እና የእዝ ኢኮኖሚ ሥርዓት ሙጭጭ ብለን መያዝ አለብን ማለት ነው የተከበሩ ዶ/ር ነጋሶ? ይህን ርዮተ ዓለም ሙጭጭ ብለን መያዝ አለብን ካሉ ደግሞ ታዲያ አሁን በአባልነትና በከፍተኛ አመራርነት የሚገኙበት ፓርቲ የሚያራምደው ርዮተ ዓለም የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ እና የሊበራል ዴሞክራሲ አስተሳሰብ አይደለም ወይ? ታዲያ  የእርስዎ ምላሽ እርስ በርሱ የሚቃረን መሆኑን አላስተዋሉምን? ካፒታሊዝም ሥርዓትን ለምን መረጡ ብለው ከኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ከተለዩ ሌላ ካፒታሊዝም ሥርዓትን የማይከተል የነፃ ገበያ ኢኮኖሚን እና የመድብለ ጠርቲ ዴሞክራሲ የማይቀበል ጠርቲ መቀላቀል ወይም መመስረት ነበር የነበረብዎት።

የተከበሩ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በአሁኑ ወቅት እየተከተሉት ያለው ስልት በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያስገኝልኛል ብለው ያሰቡትን ሁሉ ማድረግ ነው። ለዚህ ነው በቅዱስ መጽሐፍ እንደተገለፀው «ንስሀ ግቡ በወንጌል እመኑ» ተብሎ እንደተፃፈው ሁሉ አጥፍቻለሁ፣ ይቅርታ ይደረግልኝ፣ ፀፀቱ ከዕምሮዬ እስካሁን

አልወጣልኝም በማለት የተለያዩ ተማፅኖዎች እና አማላይ ቃላት ሲጠቀሙ የሚስተዋሉት። ይህ ባይሆንማ ኖሮ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት በሚረቀቅበት ወቅት የሕገ መንግስት አርቃቂ ኮሚሽን ሰብሳቢ ሆነው የሰሩ ሰው አሁን ተመልሰው ይፀፅተኛል ጥፋተኛ ነኝ ከማለት ይልቅ ያኔ የማያምኑበት ከሆነ ለምን ኃላፊነቱ ተቀበሉት? ለምን ከአስተሳሰቤና ከእምነቴ ጋር አይስማማም ብለው ኃላፊነቱን አልተውትም ነበር? ብቻ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ከኦነግ ወደ ኢ.ህ.ዴ.ድ./ኢህአዴግ ሲሸጋገሩ በኦነግ አባልነታቸው ተፀፅተው አጥፍቻለሁ ብለው እንዲሁ ከኦ.ህ.ዴ.ድ./ኢ.ህ.አ.ዴግ. ወደ አንድነት/መድረክ ሲመጡም እንዲሁ አጥፍቻለሁ እና ይቅርታ ይደረግልኝ ብለው ነው ወደፊት ደግሞ ሌላ ይቅርታ ሌላ ፀፀት እንደሚያሰሙን ከዚህ አያያዛቸው መገመት የሚቻል ይሆናል።

በዕለቱ ሌላው ተናጋሪ አቶ ስዬ አብርሃ ሲሆኑ እሳቸው የተጠየቁት ደግሞ የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 39 እንዴት ይመለከቱታል የሚል ነበር። ሆኖም አቶ ስዬ አንቀጽ 39 ስለመገንጠል ብቻ የሚያወራ ሳይሆን የብሔር ብሔሰቦችን መብት ማስከበር ዙሪያም እንደሚያብራራ አውስተው ነገር ግን መገንጠልን እንደማይደግፉት ተናግረዋል። አቶ ስዬ በወቅቱ ይህ አስተሳሰብ እንዳልነበራቸው ተናግረዋል። ትክክል ናቸው። ምክንያቱም በወቅቱ አቶ ስዬ አብርሃ አንቀጽ 39 በተለይም የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብት እስከ መገንጠል የሚለው አንቀጽ የሕገ መንግስቱ የማዕዘን ድንጋይ /cornerstone of the constitution/ ነው እያሉ በየአደባባዩ ሲገልፁና በመገናኛ ብዙሃን ሲተነትኑ እንደነበር የሚዘነጋ ጉዳይ አይደለም። እዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው ቁምነገር ግን እነዚህ አስተሳሰቦች የግድ አሁን መያዝ ያለብን ናቸው ማለት ነው ወይ የሚል ነው። ለዚህም ዋናው ምክንያት አቶ ስዬ አብርሃምም ሆነ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በፖለቲካው ዓለም ብዙ ልምድ ያካበቱ እነዚያን አስተሳሰቦች ያራምዱ በነበረበት ጊዜም ዕድሜያቸው ከወጣትነት ወደ ጉልማሳነት የተሸጋገሩበት ወቅት በመሆኑ እናም በሰከነ መንፈስ ለማሰብና ለማገናዘብ የሚችሉበት ደረጃ ላይ የነበሩ ስለሆነ ነው።

ስለዚህ በዚህ ፅሁፍ አቅራቢ እምነት ለምን ተሳሳቱ ወይም ደግሞ ለምን ይቅርታ ጠየቁ ወይም ለምን የአስተሳሰብና የአመለካከት ለውጥ አመጡ አይደለም። ተሳስቶ ይቅርታ መጠየቅ፣ ወይም አዲስ አመለካከትና አስተሳሰብ መያዝ የግድ ከስልጣን ሲለቁና ጥቅማጥቅሞች ሲጓደሉ መሆን የለበትም ነው። ጥፋት ተሰርቶ ይቅርታ መጠየቅ ያለበት በስልጣን ላይ እያሉ ነው። የአስተሳሰብና

የአመለካከት ዕድገትና ለውጥም ማምጣት ያለብን በሥልጣን ላይ እያለን ነበር፡፡ ከዚያ ከወጣን በኋላ ሁሉንም ጣቶች ወደዚያ ወደ ነበርንበት ቦታ መቀሰር ትክክል ነው ብሎ መውሰድ አይቻልም፡፡ ሆኖም የእወደድ ባይ ፖለቲካ /populist politics/ አማራጭት ዋነኛ ስልት ይኸው ስለሆነ እነ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ይህን ቢከተሉ ብዙ አያስደንቅም፡፡ ዋናው ነገር ግን ሁኔታዎችን ከምክንያትና ውጤት አንፃር የሚመለከቱ እጅግ ብዙ ኢትዮጵያውያን አሉና ሂደቱ ብዙ አዋጭ አይሆንም፡፡

ቸር ይግጠመን፡፡